# የሱፍ አበባ - አጭር ትችት

(የሱፍ አበባ፣ በሀብታሙ አለባቸው፣ አዲስ አበባ፣ 2008 ኢ.ም)

ስለ ኢ/ህ/አ/ፓ የተፃፉ ታሪኮችን አልፎ አልፎ አነብባለሁ። አብዛኛዎቹ ተረኮችና የተረኮቹ ደራሲዎች ሚና  በቅንነት የቀረቡ ሆነው አግኝቻቸዋለሁ። ለመጀመሪያ ጊዜ ጥርጣሬ ያደረብኝ የህይወት ተፈራን Tower in the Sky ሳነብብ ነው። በህይወት ድርሰት ውስጥ የሚከተሉት ተረኮች የደራሲዋን ሚና እንድጠረጥር አድርገውኛል። ኩዬራ ውስጥ ተይዛ ሳለ ወዲያው አለመገደሏ፣ ከነበረችበት እስር ቤት ለእርፍት ወጣ ገባ ማለቷ፣ የጌታቸው ማሩን ታናሽ ወንድም (የአለማየሁ ማሩን) ሚና አለማንሳቷ፣ እስር ቤት ውስጥ ሳለች ደግሞ ድንገት ሁሉን ይቅር ለእግዜር ብላ የመ/ኢ/ሶ/ን አባላትን መንከባከቧ ለአብነት የሚበቁ ተረኮች ናቸው። ከሁሉ በላይ ጠርጣሪ ያደረገኝ ግን ህይወት ለጌታቸውም ለፓርቲውም ታማኝ ሆኜ ቀጥያለሁ ማለቷ ነው፤ እነጌታቸው የግል ፍቅረኛዎቻቸውን ቀርቶ በስራ የማያገኟቸውን የቀድሞ የፓለቲካ ጓደኞቻቸውን ከፓርቲው ስራ እንዳስኮበለሉ በርካታ መረጃዎች እያሉ። "ከፓርቲው ጋር የቆየሁት አማራጭ በማጣቴ ነው" የሚለው የህይወት መከራከሪያም እምብዛ አሳማኝ አይደለም፤ ይልቁን እንዲህ ማለቷ በትግሉ የመቀጠሏን ዋጋ እጅግ የሚያራክስ ነው። በሆነ ድርጅት  ውስጥ አማራጭ በማጣት ብቻ አባል ሆኖ የቆየ ሰው በፓለቲካ ተቃራኒው እጅ ሲወድቅ ደግሞ፣ በተለይም ደርግን በመሰለ አረመኔ ሲፈተን፣ ምስጢር ቋጥሮ ለማለፍ ፅናት አይኖረውም። ይህን እንኳን የዚያ ዘመን ወጣት፣ የዛሬውም ስለያኔው ታሪክ ከሰማው እና ካነበበው የሚገምተው ነው። እናም የህይወትን ተረኮች በጥርጣሬ ለማየት እገደዳለሁ።

እንዲያም ሆኖ የህይወት መፅሀፍ ስለ ዘመኑ የፓለቲካ ህይወት ለመጭው ትውልድ ያስተላለፈው መልእክት ግዙፍ ነው።

ሀብታሙ አለባቸው ያሳተመውም "የሱፍ አበባ" ብዙ ታሪኮችን ለመጪው ትውልድ አስተላልፏል። ከህይወት መፅሀፍ ጋር የሚመሳሰልበትም አያሌ ገፅታዎች አሉት። የመጀመሪያው የወል ገፅታ የወንድ እና ሴት ፍቅረኛሞችን ታሪክ አጉልቶ ማስቀመጡ ነው፤ ለንባብ ማጣጣሚያ ከሚፈለገው በላይ። ይህ ገፅታ የኢ/ህ/አ/ፓውያን መገለጫ አልነበረም። በግል ተመክሮዬ ላይ ተመርኩዤ እንዲህ ማለት እችላለሁ፤ በተለያዩ አካባቢዎች፤ የመዋቅር እርከኖችና ተግባራዊ ተሳትፎዎች ያስተዋልኩት ፍጹም ከዚህ ተቃራኒውን ነው። ተረኩን ልቦወለድ ያላለው  ሀብታሙ አለባቸው በርግጥ በኢ/ህ/አ/ፓ ትግል ተሳትፎ ከሆነ (ያውም በሚላቸው እርከኖች) ታማኝነቱና ትልቁ ፍቅሩ ለፓርቲውና ለህዝቡ አልነበረም፤ ለግል ፍቅረኛው እንጂ። በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ይህን መልሶ መላልሶ ገልጾታል። በዚህም የኢ/ህ/አ/ፓ ታሪክ ላይ ጥላሸት ሊቀባ ሞክሯል። ኢ/ህ/አ/ፓውያን ለድርጅታቸው እና ለህዝባቸው ሲሉ ሁለመናቸውን ለመሰዋት ወደሁዋላ ያላሉ አልነበሩምን? እንዲያ ስለነበሩ አይደለም እንዴ የቤተሰቦቻቸውንና የወዳጆቻቸውን ህይወት አደጋ ላይ የጣሉት? የራሳቸውማ ህይወት የህዝቡ ስለነበረች ለትግሉ እስከሆነች ደረስ ጠፋች አልጠፋች ብለው ብዙ አልተጨነቁም። እጅግ አብዛኛዎቹ ግላዊ ፍላጎት የሚባልም ነገር አልነበራቸውምና አንድን ሴት/ወንድ ከማህበረሰቡ ከፍ አድርገው በፍትወተ ስጋ ወላፈን አልተጠበሱም። አልፎ አልፎ ባዮሎጂካል ፍላጎታቸው ያሸነፋቸው ቢገኙ እንኳ "ከብረት ዝገት ከአመላመልም ስህተት አይጠፋም" ብሎ ማለፍ ይቻላል እንጂ ኢ/ህ/አ/ፓውያን ከጓዶቻቸው ይልቅ የወሲብ ጓደኞቻቸውን  የሚያስበልጡ አድርጎ ማቅረብ ቢያንስ ሸፍጠኛነትን አሊያም ስውር ተልእኮን አመልካች ነው። በወቅቱ ላልነበረ የዛሬው እና የወደፊቱ ትውልድ የተሳሳተ ስእል እንዲያይ ማድረግ ይሆናል።

ህይወትና ሀብታሙ ሌላም የሚጋሩት አሉታዊ ነጥብ አለ፤ ለጥፋቱ ሁሉ ተጠያቂ የሚያደርጉት የተወሰኑ የአመራር አባላትን መሆኑ። እነዚያ መሪ ግለሰቦች ተሳስተው ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ከሳሾቹ የክስ ማቅለያ ነጥቦችንም አብረው ማንሳት ነበረባቸው። ለኢ/ህ/አ/ፓ ልምድ ያወረሰ ቀዳሚ ድርጅት በኢትዮጵያ አለመኖሩ፤ አለማቀፋዊው ሁኔታ ያለ ወዳጅ መቆምን ግድ ማለቱ (ከምእራቡ ኢምፔሪያሊዝምና ከምስራቁ ሪቪዥኒዝም አንዱን መምረጥ ላልፈለጉ ሁሉ)፣ ኢ/ህ/አ/ፓን እንደ ዳግማዊ ሸዋ ወይም ኒዮ ነፍጠኛ የሚመለከቱ ዘውጌ ብሄረተኛ ደርጅቶች እንደ አሸን መፍላታቸው፣ ህ/ግ/ሃ/ኤ የኤርትራ ጥያቄ እንደ ቅኝ ግዛት ጥያቄ እንዲታይለት ጫና ማሳደሩ፣ መ/ኢ/ሶ/ን ቀድሞ ቤተመንግስት ገብቶ በሩን መቀርቀሩ፣ የመሬት አዋጁ በአርሶ አደሩ ዘንድ ብዥታ መፍጠሩ፣ የሶማሊያ ወረራ እና ሌሎች ብዙ ክስተቶች በአንድ ጊዜ ተነባብረው መጋረጣቸው፣ ... ለአንድ ልጅ እግር ድርጅት ምን ያህል አስቸጋሪ እንደነበር መወሳት ነበረበት። ከዚያም ባሻገር ስለሆነው

ሁሉ ሀላፊነቱ የጋራ ነው፤ ክብደቱ እንደ አባላት መዋቅራዊ እና ተግባራዊ የተሳትፎ ደረጃ ቢበላለጥም። ወይስ "እኔ በትግሉ የተሳተፍኩት በራሴ አእምሮ ማሰብ የማልችል ስለነበርኩ እንደ ባቡር ፉርጎ ጎትተውኛል" ለማለት ነው?

የሀብታሙን መፅሀፍ የበለጠ አደገኛ የሚያደርገው በማእከላዊ ኮሚቴ ተለዋጭ አባልነቴ በቀጥታ አየሁት/ተሳተፉኩበት የሚላቸውን ታሪኮች ስምና ቦታ እየጠራ ሲናገር እውነተኛ ለማስመሰል ያለው ችሎታ ነው። ከክፍሉ ታደሰ በስተቀር በሙሉ አፍ ይህ እውነት፣ ይህ ውሸት ነው ማለት የሚችል ሰው በአሁኑ ጊዜ ባይኖርም "የሱፍ አበባ" ውስጥ ያሉ ታሪኮች ተአማኒነት እንደሚጎድላቸው የሚጠቁሙ መረጃዎች በራሱ በስራው ውስጥ ሞልተዋል። ደራሲው በንዝህላልነት ወይም በምንቸገረኝ ወይም ሳያውቅ የሚያውቅ በማስመሰል የፃፋቸው ጥቃቅን መሳይ ስህተቶችን መደርደር ይቻላል። አንድ ሰው ታሪክ ወይም ልቦለድ ለመሆኑ በግልፅ ያልተቀመጠ ፅሁፍ ሲደረድር በምንቸገረኝነት እንደመጣለት መፃፍ የለበትም። ሀብታሙ ግን እንደዚያ ስላደረገ የዘረዘራቸው ሁሉ እውነት ለመሆኑ ምን ዋስትና አለ? የሆነ ቀለም አይቶ ቀይ ወይ ነጭ መሆኑን ማስታወስ ያልቻለ ሰው አለማስታወሱን መግለፅ አለበት እንጂ በምንቸገረኝ ቀይ ነው ሊል አይገባውም። ቀለሙ ነጭ ሆኖ ቢገኝስ?

ደራሲው ኢ.ም ባለመጥቀስ ሊነሡበት የሚችሉትን አፋጣጭ ጥያቄዎች ለመቀነስ ይሞክራል። ግን እዚህም እዚያም በንዝህላልነት የተጠቀሱ አጉራዎችን (ክሌይምስ)፣ አባባሎችን፣ የአሰራር ስልቶችን እና የቦታ ገለፃዎችን ብቻ ነቅሶ በማውጣት ሌሎችንም የሁነት ገለፃዎች፣ አተረጓጎሞች እና አንድምታዎች ያለ አንዳች ጥንቃቄ እንዳዥጎደጎዳቸው ማሳየት ይቻላል። አለፍ አለፍ አድርጌ ከዚህ በታች እጠቅሳቸዋለሁ፤ በስተግራ የገፅ ማጣቀሻ ቁጥሮችን በመጠቆም።

"የማእከላዊ ኮሚቴው ተለዋጭ አባል" ነበርኩ የሚለውና አዲስ አበባ ውስጥ የነበሩ የኢ/ህ/አ/ፓ አመራር አባላትን በሙሉ በቀጥታ እያገኘ እንዳነጋገረ የሚገልፀው ደራሲ ለማመን የሚያስቸግር የማስታወስ ችሎታ ያለው ይመስላል። ከዛሬ 35 አመታት በፊት የተደረጉ ንግግሮችን በቅደም ተከተል ሲያስቀምጥ፣ ማን ከማን ጎን ተቀምጦ እንደነበር ወይም ማን ከማን ቀጥሎ እንዳወራ ሲያወሳ፣ አልፎ ተርፎም የለበሱትን ልብስ እየዘረዘረ ሲገልፅ ጥቂትም አልፈራ፡፡ አንዱ ተሰብሳቢ በንግግሩ መካከል የት ቦታ ላይ ደርሶ ሲጋራ እንደሳበ ጭምር ያስታውሳል፤ ይህ ተአምረኛ ደራሲ፡፡ በጊዜው ቃለ ጉባኤዎች ቢያዙ፣ የተያዙትም ሁሉ ሳይበላሹ ደራሲው መልሶ ቢያገኛቸው እንኳ ማን ከማን ጎን እንደተቀመጠ ወይም ማን መቼ ሲጋራ እንደሳበ የሚገልፅ ማስታወሻ አለመኖሩ ለማንም ግልፅ ነውና መፅሀፉ "ታሪካዊ" ልቦለድ መሆኑን እንድንረዳ ያደርገናል፡፡ ግን ታሪካዊ ልቦወለድም ቢሆን የነበረውን እውነታ አጣምሞ ማቅረብ ስለማይጠበቅበት ስህተተኛ ታሪኮችን መቃወም ይገባል፡፡ ይሁንና እሱ በየስብሰባው ቦታ እና በየድርጊቱ ጊዜ ነበርኩ ብሎ ያቀረባቸውን ታሪኮች ተአማኒነት በዝርዝር አልከራከርም፤ በስብሰባዎቹም ሆነ በድርጊቶቹ ላይ እንደደራሲው ምሉእ በኩልሄ ሆኜ አልተካፈልኩምና። ውስጥ አወቅ ባልሆንም በይፋ ከሚታወቁ ኢ/ህ/አ/ፓ ነክ ሀቆች ጋር የሚጣረሱ በርካታ የደራሲው ተራ ስህተቶችን ለማሳየት እወድዳለሁ። እንዲያ በማድረግም የመፅሀፉን አጠቃላይ ይዘት እና መልእክት አንባቢ እንዲታዘብ እጋብዛለሁ።

መፅሀፉ በሽፋን ገጹ አሊያም በውስጠኛ የርእስ ገጹ በግልፅ ልቦለድ/ታሪካዊ ልቦለድ መሆኑን አይገልፅም። ያላንዳች መቅድም እና መግቢያ ወደ ታሪኩ ይገባል። እንዲያ በመቅረቡም ስራውን በእለታዊ የግል ማስታወሻ ላይ እንደተመረኮዘ የቀዳሚ ህይወት ማስታወሻ (ሜሚ ወይም ባዮግራፊካል ኖትስ) መቀበል ግድ ነው።

11 ደራሲው በዚህ ገፅ ላይ ተቀጥሮ ይሰራበት የነበረው የእርሻ ሚ/ር በንጉሡ የተናቀና በደርግም ብዙ ያልተለወጠ መሆኑን ገልጾ ከዚያ መስሪያ ቤት ኢ/ህ/አ/ፓ ገላገለኝ ይላል፡፡ ስላልነበሩበት አለም በጭፍን ከመናገር መታቀብ አስተዋይነትን ይጠይቃል። እንዳሻ ፅፎ መፅሀፍ ማሳተምን ባህል ባደረግንበት ዘመን ላይ ሆንን እንጂ የንጉሡም ሆነ የደርግ አገዛዝ ኢትዮጵያን ለማዘመን መለወጥ አለባቸው ብለው ካመኑባቸው አበይት የኢኮኖሚ ዘርፎች አንዱ የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ነበር፡፡ በንጉሡ ዘመን የተቋቋመውን የ-ኤፒድ መዋቅር፣ የካዱና የዋዱን የግብርና ማእከላት፣ ወዘተ. ማስታወስ ይገባል። በዘመነ ደርግም በግብርና ላይ የሚያተኩሩ የምርት ካድሬዎች፣ በተለያዩ የአግሮ ከላይሜትክ ዞኖች የተመሰረቱ የምርምር ጣቢያዎች ነበሩ። ታዲያ የእርሻ ሚ/ር ባልደረባ የነበረው ደራሲ አባባል በግዴለሽነት የተወረወረ መሆኑን ልብ እንበል። ደራሲው ከዚህም በላይ በአንድምታ ሊነግረን ያቀደው ነጥብ አለ፤ በዚያ ዘመን ስራውን የጠላ ሰው አማራጭ ወደ ኢ/ህ/አ/ፓ መቀላቀል እንደነበር፡፡ ይህና ይህን የሚመስሉ የደራሲው ድብቅ መልእክቶች ወደ መፅሀፉ እየጠለቅን ስንሄድ ይበልጥ ግልፅ ይሆኑልናል። አብራችሁኝ ቆዩ።

እንደ ደራሲው ትረካ ኢ/ሀ/አ/ፓን መቀላቀል በጣም ቀላል ነበር። በፓርቲው እርከንም ውስጥ ወደ ላይ መስፈንጠር ይቻላል። እንዲህ ይላል፤ "በአጭር ጊዜ ውስጥ ነው የኢ/ሀ/አ/ፓን መሰላል ፉት ብዬ የወጣሁት፡፡ ... በወራት ውስጥ የአዲስ አበባን በይነ ቀጣና ተቀላቀልኩ፡፡ ... የፓለቲካ ኮሚቴ ተጠሪ ሆንኩ፡፡" ይህም ያለምንም ይሉኝታ ደራሲው በወራት ውስጥ የአ/አን ትግል ከመሩት 5 ሰዎች አንዱ ሊሆን እንደበቃ ይገልፃል። እኔ እስከማውቀው እንኳን የኢ/ሀ/አ/ፓ የርሱ ወጣት ክንፍ መሪዎችም በረጅም የተማሪዎች ንቅናቄ እና የምሁራን ትግል ውስጥ ያለፉ ነበሩ። ወደ ተደራጀ ትግል ተሻግሮ በርካታ ሀገር አቀፍ እና ዘውግ ተኮር ድርጅቶች ያፈራውን ረጅም ቀዳሚ ታሪክ የሚያውቅ ወይም የታሪኩ ንቁ ተሳታፊ የነበረ ማንኛውም ሰው - “የኢ/ሀ/አ/ፓ ማ.ኮ ተለዋጭ አባል” ይቅርና - ከላይ የተጠቀሰውን ሊፅፍ አይችልም። ይህን ስህተት የአላዋቂነት/የግዴለሽነት መዘዝ አድርጎ መውሰድ ይቻል ይሆናል። ግን በአንባቢ አእምሮ ለየት ያለ አሰር (ኢምፕሬሽን) ለመተው ታስቦበት የተባለ ሊሆንም ይችላል፤ ኢ/ሀ/አ/ፓ አልባሌ ሰዎች ከዚህም ከዚያም ድንገት ጎራ ብለው የመሰረቱት መናኛ ድርጅት እንደነበር የሚያሳይ አሰር።

12 የኢ/ሀ/አ/ፓን ዝርክርክ አሰራር ሊነግረን ከብርሃነ መስቀል ጋር በተዋወቀበት እለት ለሶስት ሰአት ከሱ ጋር ማውራቱን ይጠቅሳል። በዚያን ጊዜ እንኳን የከፍተኛ እርከን የዝቅተኛው አመራር አካላት የነበራቸውን የጊዜ እጥረት ያልተገነዘበ፣ አሊያም ሆን ብሎ ድርጅቱን የስራ ፈቶች ስብስብ ለማለት የተሰጠ ቃል ነው።

13 ደራሲው ከኢትዮጵያ ህዝብ አርነት ደርጅት (ኢ/ሀ/አ/ድ) ወደ ኢ/ሀ/አ/ፓ የተደረገውን የስም ሽግግር ጥያቄ ውስጥ በማስገባት በቀድሞ ስሙ ቢቀጥል ኖሮ የቀኞችንና የአክራሪ ብሄረተኞችን ድጋፍ ያገኝ እንደነበር ለብርሃነ መስቀል ይገልፅለታል። ብርሃነ መስቀልም በመከፋት ዘርኡ ክህሸንና ተስፋዬ ደበሳይን እንዲጠይቅ ይመክረዋል፡፡ ቶሎ መፍረድ አይሁንብኝ እንጂ እዚህ ጋ ያለው ተዋስኦ የደራሲውን የፖለቲካ ጠረን የሚገልፅ ነው፤ ጠረኑ የኢ/ሀ/አ/ፓ አይደለም፤ የዘውጌ ብሄረተኛ እንጂ። ቀኞችንና አክራሪ ብሄረተኞችን ማቀፍ የሚችል ትግል የወቅቱን የህዝብ ጥያቄ የሚመልስ አልነበረም። ደራሲው በጊዜው ክልላዊ ጥያቄን አንግበው የተነሱትና ቀኞችንም ብሄረተኞችንም ለማቀፍ ያልተቸገሩት ድርጅቶች ትክክለኛ እንደነበሩ በገደምዳማ የሚነግረን ሰው ነው፡፡ በነገራችን ላይ ቀኞችን እና አክራሪ ብሄረተኞችን ያቀፈ/የሚያቅፍ የግራ ፖሊቲካዊ ድርጅት አለ እንዴ?

14 ኢ/ሀ/አ/ፓን ጠፍጥፎ የጋገረው ብርሃነ መስቀል ኢ/ሀ/አ/ሰን ይዞ እንዳይገባ የኢሳይያስና የኦስማን ሳልህ ሳቤ ጥምረት መተላለፊያ ዘግቶበት ሁለት አመት መንገድ ላይ ማቆየቱን ይፅፋል። ደራሲው በ1960ዎችና 70ዎች በኢት/ አልነበረንምን? ካልነበረ ስለዚያ ዘመን ለመፃፍ የታሪክ ምንጮችን መመርመር አይገባውም ነበርን? ያውም ቅርስ ሆኖ የሚቀር ፅሁፍ ስለዘመኑ ማሳተም ሲነሳ? በርግጥ ኢሳይያስ አፈወርቂና ኦስማን ሳልህ ሳቤ አብረው ሰርተዋል። ሁለቱም ከጀብሃ ያፈነገጡ ነበሩ። ኢሳይያስ የሜዳውን አንጃ ሲያደራጅ፣ ኦስማን ሳልህ ሳቤ ደግሞ የርዳታ እና የውጭ ግንኙነት ሀላፊ ነበር። የሁዋለኛው ቀደም ሲልም በውጭ ግንኙነት ሀላፊነቱ ጀብሃን በመሳሪያ እና በዲፕሎማሲ ስራ ይረዳ ነበር። ግን ሻእቢያ እንጂ ኦስማን የኢ/ሀ/አ/ሰን መንገድ አልዘጋም። እንዲያውም የሰራዊቱ እርሾ ከዚህ ሰው ብዙ ርዳታ አግኝቶ ነበር፤ እስከ 1967 ኢ.ም ድረስ። መስራች ቡድኑ በሻእቢያ ርዳታ ወደ ትግራይ እንዲጓዝ ያስቻለውም፣ በመሳሪያ እና ሎጂስቲክስ ያገዘውም ኦስማን ነበር። ኢሳይያስ ኢ/ሀ/አ/ሰን በቁጥጥሩ ስር ያቆየው ካለ ኦስማን ፍቃድ ነበር።

23 ደርግ ንጉሱን ያወረደ እለት ኢሳያስ ከተባለው ጓደኛው ጋር የዋለውና ከጥቂት ሳምንታት በሁዋላ የተመለመለው የዚህ መፅሀፍ ደራሲ ወዲያውኑ ለነ ዶ/ር ተስፋዬ ደበሳይ ስለ "ፓርቲ አመሰራረትና የመደቦች አሰላለፍ ለውጥ መስተጋብር" የሚተነትን ፅሁፍ አዘጋጀሁላቸው ሲለን “ልጅ ለእናቷ ምጥ አስተማረች” አያስብልምን? ይህስ ኢ/ሀ/አ/ፓና የኢ/ሀ/አ/ፓ መሪዎች ሰብእና፣ ክሂሎትና ልምድ ያልነበራቸው አድርጎ መሳያ ቃል አይደለምን?

25 ፓርቲው ከብሩክታዊት፣ ከቀድሞ ፍቅረኛው፣ በግድ ቢያለያየውም (በፓለቲካ እምነቷ ምክንያት)፣ አሁን ደግሞ ህቡእ ከገባበት ሰፈር የአንዷን ቆንጆ ፎቶግራፍ አይቶ ልቡ እንደከዳው ይገልፃል። ይህም እንደላይኛው እኩይ የሰበካ ፈትል ነው፤ ያኔ ያልነበሩ ሰዎች “ለካ ኢ/ሀ/አ/ፓዎች እንዲህ ነበሩ!” እንዲሉ የሚጋብዝ። እውነታው ግን ሌላ ነበር፤ እንኳን የፓርቲው መሪዎች አብዛኞቹ ተራ አባላቱም የፓለቲካ ማንነቱን ከማያውቁት ሰው ጋር

አንሶላ እስከመጋራት የሚዘልቅ ግንኙነት በማድረግ አይታወቁም፡፡ እያንዳንዱ የኢ/ህ/አ/ፓ አባል ታላቅ ሀላፊነት እንደተሸከመ በሚያምንበት በዚያ ዘመን፣ እያንዳንዱ ደቂቃ ሀላፊነትን ለመወጣት እና/ወይም የፀጥታ ችግሮችን ጫና ለመጋፈጥ በሚውልበት በዚያ ወቅት፣ ፎቶግራፍ ቀርቶ በአጠገብ እና በግዘፍ ያለ ውብትም ስሜትን ይገዛል ብሎ መገመት ዘበት ነው፤ በጥምዝዝ አንጎል ታሪክ ለሚፈጥር ደራሲ ተብዬ ካልሆነ በቀር።

ደራሲው ይህን የፃፈው ኢ/ህ/አ/ፓዎችን ተልካሻ ለማስመሰል እንደሆነ ይገባኛል። ግን በዚህ የማስመሰል ሙከራ ተልካሻነት የታየው በራሱ በሞካሪው ላይ ነው። ይህን ስታዘብ አንድ ነገር ትዝ ብሎኝ ነበር። "ደራሲው" እንደኖረባቸው እና እንደተወነባቸው በሚቆጥራቸው የአብዮት አመታት ውስጥ በአንጀኞች ድርጊት የተበሳጨ አንድ ፀሃፊ የዘረፈው ግጥም ነው። ባህላዊ ስንኞችን ተጠቅሞ እንዲህ ብሎ ነበር፤

"ባንዳውን ሁሉ እኛ ስናውቀው፣
ከላሹን ሁሉ እኛ ስናውቀው፣
አንጀውን ደግሞ ማን ደባለቀው?"

ታዲያ ሶስተኛውን ስንኝ "ጋለሞታውን ማን ደባለቀው?" በሚል ተክቼ ለደራሲ ተብዬው ብዘርፍለት ይገባዋል እላለሁ። ለእለት እንጀራው ማብሰያ "በሀሜት እና ስም ማጥፋት" ዘመቻ የተሰማራ ምሁር ወይም ደራሲ ተብዬ በምግባር የለሽነት ከጋለሞታ አይሻልምና።

27 መሳለሚያ አካባቢ እንደሚገኝ የተጠቀሰውን ጋራዥ በትክክል መለየት አያዳግትም፤ እንደተባለው ከቢላል መስጂድ ጋር አጥር ባይጋራም። ጋራዡ ያኔ በከፍተኛ 6 ቀበሌ 26 የሚገኝ የወርቁ ቤተሰብ ንብረት ነው። (ወርቁ አሁን በህይወት የለም። ያኔ የኢ/ህ/አ/ወ/ሊ የንኡስ ሪጂን አባል ነበረ)። ጋራዡ አሁንም አለ፤ ሄዶ ማየት ይቻላል፡፡ በጋራዡ አቅራቢያ ኢ/ህ/አ/ወ/ሊ አንድ የሪጂን ኮሚቴ አባላቱን (ደረሱ፤ ደብረወርቅ፣ ብርሃኑ እና ?) ሙሉ በሙሉ አጥቷል፤ በሁለተኛው ዙር አሰሳ የመጀመሪያው ቀን። እንዲያ በመሆኑም ቦታውን የበለጠ በመመርመር ወደፊት ተጨማሪ መረጃዎችን መሰብሰብ ያስፈልግ ይመስለኛል። ምናልባትም ብዙ የተደበቁ ምስጢሮች ይገለጡልን ይሆናል፡፡

31 " ... ሰነዶቹ ጠፉ ማለት ኢ/ህ/አ/ፓ አይኖቹን አጣ ማለት ነው ...." ይላል ለደራሲው ሁሉን እያዘረ የሚያስጎበኘው ኢሳይያስ የተባለ መልማይ ጓደኛው። ለምን ይሆን ኢሳይያስ ለደራሲው የወታደራዊ ክንፍ አባላትን ማንነት የሚገልፅለት? ለምንስ ነው መአት የሚስጢር ሰነዶች የሚያሳየው? የትኛው ምስጢራዊ ድርጅት ነው የተፃፈ የአጠቃቀም መመሪያ (ማኑዋል) እያነበበ የሚታገለው? የአደፍርሷ ማኑዋል ስትጠፋበት የተነገረውን ማስታወስ ያቃተው ደራሲ፣ ከዚህ ዝንጋታው ተነስቶ እርሱ በምናቡ የነደፈው የትግል ፈለግ ማኑዋል ሲጠፋ ሚሊዮኖች የትግል መንገዱ እንደጠፋባቸው ያመነ ይመስላል።

31 – 32 የከተማውን ታጣቂ ክንፍ አባላት "ፈዳይኖች" መሪያቸውን ደግሞ "ጠርናፊያቸው" ይላል ኢሳይያስ፡፡ እነዚህን የአረብኛ እና ትግሪኛ ቃላት ኢ/ህ/አ/ፓ ቢያንስ በአ/አ አልተጠቀመባቸውም፡፡ ሁለተኛው ቃል ህ/ወ/ሃ/ት አዲስ አበባ ከደረሰ በሁዋላ የተለመደ ነው፤ ከህ/ወ/ሃ/ት ጋር ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ግንኙነት ባላቸው ትግሪኛ ተናጋሪ ባለሆኑትም ሰዎች ዘንድ ታዋቂ ሆኖ። ደራሲው ራሱን በገፅ 1 ላይ እንደገለፀው አፉን በአማርኛ የፈታ የባህር ዳር ተወላጅ ከሆነ እነዚህን ቃላት የተማረው ከ1983 ኢ.ም. በሁዋላ ነው፣ አሊያም ስለማንነቱ የተሸሸገ ነገር አለ።

52 ስዩም ከበደ የኢ/ህ/አ/ፓ ታጣቂ ክንፍ ዋና ኮማንደር ነበር ይለናል፡፡ ምናልባት ደራሲው በኢ/ህ/አ/ፓ ውስጥ ይበልጡን ግን በአንድ ሌላ ድርጅት ውስጥ ተሳትፎ የገጠሩን ሰራዊት አደረጃጀት በወሬ ወይም አብሮ በመኖር ሳያውቅ አይቀርም እላለሁ። የከተማውን ታጣቂ ክንፍ አደረጃጀት ግን የሚያውቀው አይመስልም። ስለ ዋና ኮማንደር ያለውም ከገጠሩ ተመሳሳይ ሳይሆን አይቀርም በሚል ድፍረት ነው። የከተማውን የታጠቀ ክንፍ አደረጃጀት በፓርቲውም ሆነ በክንፍ ድርጅቶቹ በቀጥታ እና ከቀጥታ በላይ ባሉ መዋቅሮች የሰሩት ጠንቅቀው ያውቁታል፡፡ የኮማንደሮች እርከን በሪጂን ደረጃ አብቅቶ የነሱ ፀሃፊ አሀዶቹን ከንኡስ ቀጣናው የፖለቲካ መዋቅር ጋር በነጠላ ግንኙነት ያስተሳስራል። የፀሃፊው ሚና በኮማንደሮቹ አማካይነት የንኡስ ቀጣናውን የትጥቅ እንቅስቃሴ ማስተባበር፣ የተቀናጀ ተልእኮ ሲኖር ከንኡስ ቀጣናው ወደ ሌላ ንኡስ ቀጣና ተዋጊዎች የሚላኩበትን ሁኔታዎች ማመቻቸት፣ የቅንጅቱን ጊዜያዊ ኮማንደር በመሰየም ውሳኔ ማስተላለፍ ነበር። ራሱ

በቀጥታ የሚያዝዘው አሀድ አልነበረውም፡፡ እሱ የኮማንደሮቹ ፀሃፊ ሆኖ የቀጣናው የመከላከያ ኮሚቴ አባል ይሆናል፡፡ ይህ ማለት የሪጂኖቹ የትጥቅ እንቅስቃሴ መሪ ሆኖ ወደ ላይ ከቀጣናው ጋር የሚያገናኝ ነገር ግን በሪጂን እና በቀጣና መካከል ካለው የንኡስ ቀጣና የፓለቲካ አካል ጋር የተሳሰረ ሰው ማለት ነው፡፡ የቀጣናው የመከላከያ ኮሚቴ ፀሃፊ የቀጣናው ፓለቲካ ኮሚቴ አባል ሲሆን ውሳኔዎችን ከበይነ ቀጣናው የፓለቲካ ኮሚቴ በኮማንደሮቹ ፀሃፊ አማካይነት ወደ ታች እንዲተላለፉ ያደርጋል፡፡ ስለዚህም ባልተማከለው የትጥቅ እንቅስቃሴ የከተማውን የታጠቀ ክንፍ በሙሉ የሚያዝ ዋና ኮማንደር ከየት መጣ?

53 ስለ ስዩም ከበደ ጠባቂዎች (ቦዲ ጋርድስ) ሲያወራ በትክክል አስቦበት የዋሸ አይመስለኝም፤ የውሸቱ ግብ ምንም ይሁን ምን፡፡ ለስዩም ጠባቂዎች ከተመደቡ እነ ተስፋዬ ደበሳይ እና ዘርኡ ክህሸን ለምን ብቻቸውን እንደተንቀሳቀሱ አልፃፈምና፡፡

58 የፓርቲው ማእከላዊ ኮሚቴ "ፓሊስ" የሚል ቃል በመስማቱ ብቻ እንደተበተነ ይገልፃል፡፡ ፓሊስ በቦታው ስላለፈ ብቻ ነው የተበተኑት? በመከበብ ላይ ሳሉ ከነበረ ሁሉም ነገር ያለ ፍልሚያ እንዴት በቀላሉ አለቀ? ደራሲው የፃፈውን ቃል ከመጫጫሩ በፊት እንዲህ ያሉ መሰረታዊ ጥያቄዎችን አንስቶ መልሳቸውን ማወቅ እንዳለበት ግንዛቤ እንኳ ያለው አይመስልም። ማለት የፈለገው ነገር አለ፤ የኢ/ህ/አ/ፓ ማ.ኮ በቀላሉ ሊገኝ የሚችልበት ቦታ ሁሉ ይሰበሰባል፤ ኮሽ ካለ ደግሞ ወዲያውኑ አሞራ እንዳየ የጫጮቶች ጥርቅም ይበተናል። ይህን ተላላ አንባቢዎቹ ከተቀበሉለት ይረካል። ጠርጣሪና መርማሪ አንባቢዎች፣ ወይም የዚያን ዘመን እውነታ የሚያውቁ ታዛቢዎች ለሚያነሱት ጥያቄዎች መልስ የመስጠት ሀላፊነትም ሆነ የሞራል ግዴታ የለበትም። እንዲህ አይነቱ የስነምግባር እና የሙያ እሳቤ ለራሱ እና ለሰነፅሁፍ ሙያ የሚቆረቆር ደራሲን እንጂ እንደ ተስፋዬ ገብረአብ ያለን ቅጥረኛ እና ካድሬ ደራሲ አያስጨንቁም። ሀቅ እና ልቦለድን ደባልቀው ታሪካዊም ሆነ ዘመነኛ ግለሰቦችን እና ድርጅቶችን ይክባሉ፣ ያዋርዳሉ፣ ስም ያጠፋሉ፣ በማህበረሰብ ውስጥ ጥላቻ እና ግጭት ያፋፍማሉ፤ ያውም በሚጥም ቋንቋ፣ በሚስብ ትረካ።

67 እዚህ ላይ ጎላ ሚካኤል ተብሎ የተጠቀሰው ቦታ በዚያ ዘመን አጠራር ከፍተኛ 7 ቀበሌ 24 የሚባለው ነበር። ቀደም ሲልም ሆነ ከአብዮቱ በሁዋላም "አዲሱ ሚካኤል" ይባላል። በርግጥ አ/አ ውስጥ ጎላ ሚካኤል የሚባል አካባቢ አለ፤ በጎርደሜና በተክለሃይማኖት መካከል ያለው ሰፈር ነው፤ (ከአሁኑ ኢሚግሬሽን መ/ቤት ወደ ተከለሃይማኖት ሲኬድ በስተቀኝ ያለው)፡፡

69 ሴት ፓሊሶችን በቅባት እና መሰል ስጦታዎች መደለል ያልተለመደ ነበር። ደግሞም ብዙ ተመልካች በሚገኝበት የፍተሻ ቦታ እንዲያ ማድረግ የሚቻል አልነበረም።

71 አዎ በራዛ ዘመቻ ሸዋ የሱሉልታ ገበሬ አልተሳተፈም።

75 በጥር ወር ያገባው ወጣቱ ገበሬ በሱሉልታ መሬት ባያገኝም መንስኤው መሬቱ ለሀብታሞች በመሰጠቱ አልነበረም። አሁን ሱሉልታና ሙሎ ተብሎ ለሁለት በተከፈለው ወረዳ 88 የገበሬ ማህበራትን የመሰረቱት የተማሪ ዘማቾች ነበሩ። እነርሱ ህዝቡን በማሳተፍ ፍትሃዊ ነው ሊባል የሚችል የመሬት እደላ አከናውነዋል። የእደላው ምጣኔ በዋናነት የቤተሰብ ብዛትን መሰረት ያደረገ ሲሆን ላላገቡ ወጣት ወንዶች በቀጥታ በባለቤትነት የሚይዙት መሬት አልተሰጠም። ጎጆ ሲቀልሱ ግን ቤተሰቦቻቸው ከድርሻ መሬቶቻቸው ላይ የሚገባቸውን ያህል ከፍለው ይሰጧቸው ነበር። ስለዚህም በጥር 1968 ኢ.ም ያገባ ወጣት በመጋቢት እና ሚያዝያ 1967 ኢ.ም ተሸንሽኖ ከተከፋፈለው የቤተሰብ ይዞታ አነስም በዛ ድርሻውን ሳያገኝ አልቀረም። አነስም በዛ ሊወቀስ የሚችለው ቤተሰቡ እንጂ በወቅቱ የነበረው አገዛዝ የተከተለው ፓሊሲና አሰራር አይደለም፤ አይውገረገር!

88 ከተሞችን ለቅቆ በገበሬው መሃል የትጥቅ ትግል ማካሄድ የጫጉላ ሽርሽር አይደለም። በፓለቲካ ስራ መቀደም አለበት። ይህም ጊዜን ይጠይቃል። ኢ/ህ/አ/ፓ ቀደም ሲል ጀምሮ ያነሳቸውን ጥያቄዎች በገጠርም በከተማም በህዝቡ ዘንድ ማስረፅ ቢሞክርም የከተማው ቀድሞ የሄደበት አያሌ ምክንያቶች ነበሩ። እሱን እዚህ ላይ ቆም አድርጌ የገጠሩን ብቻ ላራምድ ቢልም የጠላት ዱላ ከከተማው ባላነሰ ጥንካሬ መከተሉ አይቀሬ ነበር። ኢ/ህ/አ/ፓ እንደ ዘውጌ ብሄረተኛ ድርጅቶች በአንዲት የዲሞክራሲ ጥያቄ ላይ ብቻ አላተኮረም፤ ያልተወሳሰበ

ጥያቄም ይዞ አልተነሳም። "አማራ ጨቆነህ፤ በቋንቋህ እንዳትማርና እንዳትሰራ አደረገህ፣ አንተን ይንቅሃል፣ በማንነትህ እንድታፍር ያደርገሃል፣ እሱ ባይበዘብዝህ ኖሮ እጅጉን በበለፀግህ ነበር" ወዘተ. ማለትና የዲሞክራሲያዊ መንግስትን ይዘትና የአመሰራረቱን ሂደት ማስተማር፣ ፍትሃዊ የሀብት ክፍፍል እንዴት እንደሆነ ማሳየት፣ አገሪቷን ወደ ላቀ የኢኮኖሚ እድገት ለማምጣት እንዴት እንደሚቻል ማስተማር፣ ከብሄረተኝነትና ከትምክህተኝነት የሚነሡትን ቅራኔዎች የመፍቻ ዜደዎችን ሚዛን ጠብቆ መራመድ፣ በሁዋላ ቀሩ የአስተሳሰብ እሴት ውስጥ ሴቶች ወደ የሚገባቸው ቦታ እንዲደርሱ ማስቻል፣ ወዘተ. በአጠቃላይ ከባድ ሚና ሆኖ ሳለ ወደ አርሶ አደሩ ማድረሱ ደግሞ ይበልጡን አስቸጋሪ ነበርና የገጠሩ ትግል በተፈለገው ፍጥነት፣ የቦታ ስፋት እና ግዝፈት አልተካሄደም። ለዚህ ሁሉ አቀፍ ትግል ደግሞ ጊዜ ትልቁ ገኘ ፋክተር ነበር። ኢ/ህ/አ/ፓ ወደ ገጠር አምርቶ ስር እስከሚሰድድ ቆሞ የሚያንቀላፋ ጠላት አልጠበቀውም። ድርጅቱን በማሰናከል ረገድ ከጠላት ፍጥነት ይልቅ በውስጡ የተፈጠረው አንጃ እጅና እግሩ ላይ ተንጠልጥሎ በማወክ የአበንሳውን ድርሻ ወስዷል።

151 "ሻለቃ ሽታዬ ደስታን ላስተዋውቅህ ነበር …"። ይህ ኢ/ህ/አ/ፓን እንደ እድር ወይም ሰንበቴ ስብስብ የሚያቀርብ አባባል ነው። አባባሉን የየዋህ ጥፋት ብንለው እንኳ ኢ/ህ/አ/ፓን ካለማወቅ የመነጨ መሆኑን አስረግጠን መናገር እንችላለን። በርግጥ ፓርቲውን ለማጣጣል በይሁንኝ ተብሎ ይሆናል። መፅሀፉ ከሚጀምርበት እስከሚያበቃበት ገፅ እንደሚገልፀው ከሆነ አንዱ የማእከላዊ ኮሚቴ አባል የማያውቀው ሰውና ቦታ የለም፤ ስልክም አዘውትሮ ይጠቀማል። ጓዶች በየአጋጣሚው ተደብቀውም ቢሆን ይተያያሉ። ምስጢርና የግለሰብን ማንነት የማወቅ ጉጉታቸው ትልቅ ነው። … ይህ ሁሉ ግን የኢ/ህ/አ/ፓም ሆነ የማንኛውም ህቡእ ድርጅት መለያ መሆን አይችልም።

184 "ገበርዲን በኮት ስር የሚለበስ አጃቢ የውስጥ ልብስ ነው" በማለት ለአዘቦት በአረንጓዴ፣ በግብዣ ቀን በቡላ ቀለም የሚለበሰውን የከፍተኛ ወታደራዊ መኮንኖች ልብስ ከሰዴሪያ ጋር የለዋወጠው በድፍረት ነው።

191 ኢ/ህ/አ/ፓ ለሰላማዊ ትግሉ በቂ ትኩረት አልሰጠም ብሎ ሲከስስ በበርካታ ቦታዎች ላይ ፓርቲው ወደ ወልቃይት ሂዶ የትጥቅ ትግል ማካሄድ ነበረበት እንጂ እዚህ ከተማ ውስጥ ቁጭ ብሎ መጮህ አልነበረበትም ከማለቱ ጋር እንደሚጋጭ አላሰተዋለም። ደግሞም በሰሜን ሸዋና በሲዳሞ (ገፅ 126) ለድርጅቱ የትጥቅ ትግል ቤዞችን ለመፍጠር የተደረጉትን ሙከራዎች "እውር ቢሸፍት ጓሮ ድረስ ነው" እያለ መልሶ መላልሶ ሲያጣጥል ለትጥቅ ትግል ወሳኝ የሚባሉ የቦታ መምረጫዎችን በመልክአ ምድር እና ከማእከል ርቆ በመገኘት ወስኖ ይሆን?

216 "የሰደድን ጋዜጣ በአደፍርስ ቀድተን … " በማለት አደፍርስ እንዴት እንደሚሰራ ፈፅሞ አለማወቁን ገለፀ። አደፍርስ የፎቶ ኮፒ ማሽን ሳይሆን ስቴንስል ላይ የተቀረፀን ፅሁፍ የሚያባዛ ነው።

225 አዲስ አበባ ስድስት "በይነ ቀጠና" እንዳለው ይገልፃል። "ቀጠና" ያለውን "ቀጣና" ብዬ ባርምለት እንኳን ከደራሲው ዝንኩር የቃል አጠቃቀም የዘለለውን የጭብጥ ስህተት ማለፍ አልችልም፤ በፓርቲው መዋቅር ውስጥ አዲስ አበባ በአራት ቀጣናዎች የተከፈለ አንድ በይነ ቀጣና ነበርና። ስለዚህ ደራሲው እንኳን በፓርቲው በክንፍ ድርጅቶቹ የአመራር ደረጃ መስራቱ ያጠራጥራል።

277ቀቀ የፎኮይዝምን ትርጉም ከገፅ 277 ጀምሮ መላልሶ ሲገልፅ ተራ ነፈሰ ገዳይነት ነው ብሏል። የፎኮይዝም አይነተኛ መገለጫ ግን ተራ ነፈሰ ገዳይነት አይደለም፤ ህዝብን ያላሳተፈ፣ እንዲያውም ከህዝብ የተደበቀ የትጥቅ ትግል መሆኑ እንጂ።

230 የእንግሊዛዊውን መምህር - ሞርተን - የኢ/ህ/አ/ፓ አባልነት አጠያያቂ ያደርጋል፤ የሶሻሊስት ፓርቲን አለማቀፋዊነት እየተፈታተነ።

231 "ዶ/ር ተስፋዬ ደበሳይ የኤርትራ ጥያቄ የቅኝ ግዛት ጥያቄ ነው ብሎ ፈረመ" ሲል እንደዚያማ ቢሆን ኖሮ ኢ/ህ/አ/ፓን ከሻእቢያ ምን እንዳጣላው ራሱን መጠየቅ ነበረበት።

259ቀቀ ስለ ቶዮታ ሃይሉክስ ሲገልፅ ማንኛውንም ነገር ያለምንም ጥንቃቄ መፃፉ ገሃድ ይወጣል። በዚህ ስም የሚጠሩ የቶዮታ መኪና ሞዴሎች የተፈበረኩት ከ1990ዎቹ እ.ጎ.አ ጀምሮ ነው።

269ቀቀ በኢ/ህ/አ/ፓ የተገደሉ ሰዎች ርምጃ የተወሰደባቸው በተስፋዬ ደበሳይ እና በዘርኡ ክህሸን ውሳኔ ብቻ እንደሆነ ያሰምርበታል። እንደዚያ ከሆነ ይህንን በቀጥታ ያወቁ ሁሉ ተጠያቂ ናቸው፡ የማእከላዊው ተለዋጭ ኮሚቴ አባል ከነበረ እሱንም ይጨምራል። ነገሩ ግን እንዲህ አልነበረም። አንድ ለኢ/ህ/አ/ፓ ደህንነት አስጊ የሆነ ሰው አስጊነቱ በህዋስ/መሰረታዊ ኮሚቴ/ንኡስ ሪጂን ኮሚቴ ጥቆማ ለበላይ አካል ይገለፃል። ይህ ጥቆማ ቢያንስ እስከ በይነ ቀጣና ኮሚቴ እንደሚደርስ በውስጥ አወቆች ይገለፃል። የመጀመሪያው ርምጃ ግለሰቡ/ቧ ከአድራጎቱ/ቷ እንዲቆጠብ/እንድትቆጠብ በተለያየ መልክ ተደጋጋሚ ማስጠንቀቂያ ማድረስ ነው። ካልተቆጠቡ ምን ማድረግ እንደሚገባ ለመወሰን በይነ ቀጣናው ለዚህ ተብሎ በተቋቋመ ፍ/ቤት ይከስሳል። ፍ/ቤቱ ለተከሳሹ ጠበቃ ያቆማል። ከዚያ ሞት ቢፈረድበት ውሳኔው በፓለቲካ መዋቅሩ በኩል ለኢንተለጄንስ አካሉ ይተላለፋል። የኢንተለጄንስ አካሉ መረጃ ሰብስቦ እርምጃ እንዲወስዱ ለተመደበ/ቡ የጥቃት አሀድ/ዶች አዛዥ በፓለቲካ መዋቅሩ በኩል ያደረሳል። ልብ ይሏል፣ ይህ ኢ/ህ/አ/ሰ በተንቀሳቀሰበት የገጠር ቦታዎች ብቻ ሳይሆን የፓለቲካ መዋቅሮች በዳበሩባቸው የከተማ ክልሎችም የተፈፀመ አሰራር ነው። ሰዎች ከበይነ ቀጣና ኮሚቴ እውቀት ውጭ የተገደሉባቸው አጋጣሚዎች ቢኖሩ ወይ በስህተት የተፈፀሙ አሊያም ድርጅታዊ ግንኙነቶች ተቆራርጠው የየአካባቢው ሀይላት ራሳቸውን ለመከላከል ከተገደዱባቸው ከ1970 በሁዋላ የተወሰዱ ርምጃዎች ብቻ ነበሩ።

271 ሀብታሙ ስለ ቀድሞ ፍቅረኛው፣ ብሩክታዊት፣ የሚሰጠው ገለፃ የሸዋሉል መንግስቱ የምትባለውን ጋዜጠኛ ጠቋሚ ይመስላል። ተገደለች የሚለው በተራማጅ ቤተመፃፍት ውስጥ ነው (አራት ኪሎ መሆኑ ነው)። የገለፃት በርግጥ የሸዋሉል ከሆነች የሞተችው ገዳም ሰፈር አካባቢ ነው። ሆነችም አልሆነች አንዲት በመሳለሚያ አካባቢ (ዞን 4) የምትኖር የጥቃት መከላከያ አሀድ አባል ወደ አራት ኪሎ (ዞን 1) እንደ ቀልድ ሄዳ በአንድ የ14 አመት ልጅ አታስገድለም። ጌታቸው ማሩም የትኛዋ ቆንጆ ልጅ እንደሆነች መለየት አይችልም። እንኳን የማእከላዊ ኮሚቴው አባል ጌታቸው ማሩ፣ ሌላ በማናቸውም የታችኛ እርከን የሚገኝ ፓለቲካ ኮሚቴ አባል የሚያውቀው መረጃ ቢበዛ ለዚህ የተሰማራው አሀድ የሚጠራበትን ቁጥር ብቻ ነው።

273 ፍቅሬ መርእድ የተገደለው በእርግጥ በእቅድ አልነበረም። በእዚያ እርምጃ ላይ ደራሲው ደጀኔ በማለት የሚገልፀው ግለሰብም ተሳትፏል። የግድያ ርምጃው እንዲወሰድ የገፋፋውም እሱ ነበር። ይሁንና በእለቱ ይትባረክ ህዝቅያስ መሳተፉን እጠራጠራለሁ። ምክንያቱም ኮማንደሩ ብቻ በፓለቲካው መዋቅር ውስጥ ከወደ ላይኛው እርከን ሲመጣ የተቀሩት ወታደሮች የነበሩ ይመስለኛል። ይትባረክ ተሳተፈም አልተሳተፈ መ/ኢ/ሶ/ኖች ተሳትፏል የሚል እምነት ስለነበራቸው በፀኑ ተከታተሉት። በአካል ከሚያውቁት ጥቂት የመ/ኢ/ሶ/ን አባላት አንዱ የሆነው ነገደ ጎበዜ በአንድ የአዲስ አበባ መዝናኛ ቤት ውስጥ አሰይዞታል። በሁዋላም ተገደለ።

279 የኢ/ህ/አ/ፓን የትግል ስልት መልሶ መላልሶ ከኮነነባቸው ምክንያቶች አንዱ በባህሉ ውስጥ ተቀባይነት ያልነበረውን ከሁዋላ አድብቶ የመግደል ርምጃ ነው። "እስቲ ይዋጣልን" የሚል የፍልሚያ ጥሪ ለመንግስት ማድረግ ነበረበት ለማለት ይሆን? ወይስ የፓርቲውን ሃጢአት ዝርዝር በሆነ ባልሆነው ለማርዘም?

282 የመሳሪያ አሰሳ መኖሩን ደራሲው ከሰፈር አብዮት ጥበቃ ሰምቶ ለፓርቲው እንዳሳወቀና ፓርቲው እስከዚያ ድረስ ይህ መረጃ እንዳልነበረው ይጠቅሳል። ደራሲው ወር እና አ.ም. ባይጠቅስም ይህ እንግዲህ በመጋቢት ወር 1969 ስለሆነ "ኧረ ተው!" ልለው ይገባኛል። በመ/ኢ/ሶ/ን እና በደርግ የደህንነት መዋቅሮች ውስጥ የተሰገሰጉት ኢ/ህ/አ/ፓውያን ገና ባልተነኩበት በዚያን ወቅት ይህንን መረጃ አንዱ የቀበሌ አብዮት ጥበቃ አባል ለዚያውም አንዱ ብቻ መረጃ ሰጠ ማለት ከአላዋቂነት በሚመነጭ ድፍረት መዘላበድ ነው። ደራሲው ስለ ድርጅቱ ያለውን ቁንፅል እውቀት ተገንዝቦ ትንሽ ቆም ብሎ ቢያስብ ኖሮ ይህንን ግድፈት ባልፈፀመ ነበር። ግን ቃሉ ፓርቲውን ለማኮሰስ በይሁነኝ የተሰጠ ይመስላል፤ ኢ/ህ/አ/ፓ በድቅድቅ ጨለማ ውስጥ የሚንከላወስ ነበር የሚል አንድምታ በአንባቢ አእምሮ ለማሳደር።

292 ኮ/ል ተካ ቱሉ በኢ/ህ/አ/ፓ እንዳይገደል የሰፈሩ ሰዎች የተከላከሉለት አድብቶ መግደል በኢት/ ባህል ስለማይወደድ መሆኑን ይገልፃል። ተካ ቱሉ በኖረበት የያኔው ገጠራማው የቡራዩ መንደር ኢ/ህ/አ/ፓ ወደ ሰፈሩ ጠጋ ብሎ ለመግደል የነበረው እድል ወደ ዜሮ የተጠጋ ሲሆን መንገድም ላይ ለማጥመድ ምቹ ቦታዎች ስላልተገኙ የፓርቲው የጥቃት አህድ ያደረጋቸው ተደጋጋሚ ሙከራዎች ወደ ርምጃና መፋጠጥ አድገው አያውቁም። በተካ ላይ የወጣት ሊጉም አህዶች ያደረጉት የመግደል ሙከራ ወደ ተግባራዊ ርምጃ አድጎ አያውቅም። እናም በኢ/ህ/አ/ፓ እና በህዝቡ መካከል የተፈጠረውን መፋጠጥ ሀብታሙ ከየት እንደሰማው አላውቅም።

295/298 ደራሲው የታሪክ እና የሁነት ጭበጦችን በንዝህላልነት ከመፃፉ የተነሳ የወቅቱን እውቅ የደርግ ግድያ ዜና አንባቢ አሰፋ አያና ይለዋል፤ አሰፋ ይርጉ በማለት ፋንታ። እንደዚሁ "የወንድ ልጅ እናት ታጠቂ በገመድ፣ ልጅሽን አሞራ እንጂ አይቀብረውም ዘመድ" የሚለውን በተለያዩ ሰዎች የተዜመ የሽለላ ግጥም ያዜመው አያሌው መስፍን ነው ይለናል። በወቅቱ ይህን በማዜም ይታወቅ የነበረው ግን ካሳ ተሰማ ነበር።

298ቀቀ ተረኩ የጊዜን ቅደም ተከተል ልብ ሳይል፣ ምናባዊውን ከእውናዊው ሳይለይ ዝብርቅርቅ እና ቅይጥ ሆኖ ቀርቧል።

307/320 ከንዝህላልነት ወይም መሳለሚያ የሚባለውን የአዲስ አበባ አካባቢ ካለማወቅ የተነሳ የሚገርሙ የጉዞ መስመሮች ደራሲው ይገልፃል። ከመሳለሚያ ወደ አየር ጤና (ገፅ 307) እንዲሁም ከመሳለሚያ ወደ ጉለሌ (ገፅ 320) የሄደባቸው መንገዶች በፍጹም ሎጂካል አይደሉም።

308 በ1969 ኢ.ም ፕላስቲክ ወንበር በኢት. ነበርን?

310 "አረብኛ ተናጋሪውን የጀበሃ ሰው እብናት ታገኛለህ፤ አስተርጓሚ ሌላ የጀበሃ ሰው ከአ/አ ይዘህ ትሄዳለህ" ብሎ መፃፍ "ኢ/ህ/አ/ፓ ከጀበሃ ጋር ያለውን ቁርኝት" ለመግለፅ የተፈበረከ አነጋገር እንጂ በገጠሪቱ ደቡብ ጎንደር፣ ለዚያውም የፓለቲካ ትኩሳቱ በደመቀበት የበለሳ አካባቢ፣ አረብኛ ብቻ ለሚናገር ሰው ይቅርና ጎንደሬ ላልሆነ አማርኛ ተናጋሪም ቢሆን አስቸጋሪ የፀጥታ ሁኔታ ነግሶ ነበር። ለዚያውስ ጀበሃ ውስጥ ብዙ አማርኛ ተናጋሪዎች እያሉ ለምን አረብኛ ተናጋሪው ተመረጠ? ደራሲው እንደ ደርግ ሁሉ ኢ/ህ/አ/ፓንና ጀብሃን "የአረብ ቅጥረኞች" ቢል አይቀልለውም ነበር?

315 እነ ኢንጂኔር ኡስማን ከግንደበረት ራቅ ያለ ቦታ ተወስደው ተረሸኑ የሚለውን እንደ ከተባ ስህተት ወስጄ የደራሲውን ያልተጣራ ወሬ የማውራት አባዜ በመታዘብ አልፈዋለሁ፤ ትክክለኛውን የቦታ ስም ብጠቁም "ከላም በረት ራቅ ያለ ቦታ" የሚለው ሀረግ በአ/አ ውስጥ የሌላ ሰፈር ስም እንድጠራ ያስገድደኛልና።

316/330 ጎይቶም ለባሲ መቼ ነው የተገደለው? ደራሲው ጊዜውን ባይጠራም በተጠቀሱት ገጾች ላይ የሚያወሳው ታሪክ የ1969 ኢ.ም ነው። ጎይቶም ግን እስከ ታህሳሳ 1970 ኢ.ም አለመገደሉን ለማሳወቅ በሬድዮና ቴሌቭዥን ቀርቦ መታየቱን መጥቀስ ይበቃል።

330 መ/ኢ/ሶ/ን በአ/አ ት/ቤቶችና ሰፈሮች ውስጥ ራሳችሁን አጋልጡ ብሎ አያውቅም። እስከዚህ ያለው ተረክ የ1969 ሲሆን መ/ኢ/ሶ/ን የነበረው ሚና ማፈን፣ ማሰቃየትና መግደል እንጂ በመድረኮች ላይ የበላይነት አግኝቶ ራሳችሁን አጋልጡ ማለት አልነበረም። አዲስ አበባ ውስጥ ራሳችሁን አጋልጡ ማለት የመጣው ከታህሳስ 1970 አጋማሽ ጀምሮ ሲሆን መ/ኢ/ሶ/ን በነሀሴ 1969 አጋማሽ በደርግ በመመታቱ በእኩይ እንቅስቃሴው አልተሳተፈም። በ1970ው የደርግ አፈና እና ጭፍጨፋ የተሳተፉት ከፈረሰው መ/ኢ/ሶ/ን ወጥተው እንደምንም ከደርግ ጋር የተጣበቁ ግለሰቦች እንጂ ድርጅቱ አልነበረም።

334 "ባደግሁበት አካባቢ ባህል ሴት ልጅ .... በደም ምልልሰ አትገደልም፡፡ ... ብሩክታዊትን የገደሏት በዚህ የጭካኔ መንፈስ አይደል?" ይላል ሀብታሙ፤ ኢ/ህ/አ/ፓን በአንድ በኩል በደም የተሳሰሩ ሰዎች ስብሰብ ለማስመል፤ በሌላ በኩል ደግሞ ፓርቲው የፈፀማቸው የግድያ ርምጃዎች ከሚሰነዘርበት ጥቃት ራሱን ለመከላከል የተወሰዱ

አልነበሩም፣ እንዲያውም ተራ የበቀል ግድያዎች ነበሩ ለማለት፡፡ የሀብታሙ አባባል ተጨማሪ መልእክት ያዘለ ነው፤ ኢ/ህ/አ/ፓ በባህላዊ እሴቶች ከለላ ደካማ እና ተሰባሪ የሆኑ እንስቶችን ይገድል ነበር ብሎ አንባቢ እንዲያስብ ማድረግ፡፡ ይሁንና የማ.ኮ ተለዋጭ አባል ነበርኩ ባዩ ግለሰብ በዚህ አባባሉ አሳፋሪ የአስተውሎ ህፀፅ ይገልጣል። ኢ/ህ/አ/ፓም ሆነ ሌሎች የኢት/ ድርጅቶች በዚያ ወቅት በፓለቲካ እና ወታደራዊ ሚናቸው አንቱ የተባሉ ሴቶችን አብቅለው ነበር። እነዚያ ሴቶች በድርጊታቸው ከወንዶች በተለየ አይን የታዩባቸው አጋጣሚዎች ከነበሩ ምክንያቱ ከወንድ ትምክህተኝነት አያልፍም። ታዲያ ሀብታሙ ይህን ማስተዋል ያቃተው ለአንዲትም ወር ያልተለየው የሴት ቀሚስ ጋርዶት ይሆን?

338 የእብናትን ተልእኮ ያደረሰችው አበበች አብሯት የሚጓዝ ፍቅረኛዋን የሚመለከት ትእዛዝ ይሰጣታል። "የሰመረን እያንዳንዱን እንቅስቃሴ ተከታተይው" ትባላለች። (ሰመረ የደራሲው ኮድ ስም መሆኑ ነው።) እሱ ደግሞ በበኩሉ የመጣበት ጉዳይ አልሳካ ማለቱን እየለየ ሲሄድ ሰላይ እንደተመደበበት መረዳቱን ይገልፃል፡፡ ይህ ድርብርብ ክስ - አባላትን መሰለልና ለዚያም አላማ የግል ፍቅረኛዎቻቸውን መመደብ - ደራሲው በዚህ ድርጊቱ ከሚታወቅ ሌላ ድርጅት መምጣቱን ወይም በዚያ ድርጅት ይህንን ፅሁፍ እንዲፅፍ መታዘዙን እንድጠረጥር ያደርገኛል፡፡ “ሌባ እናት ልጇን አታምንም” የሚሉት በ“ደራሲ”ው ደረሰና እንጂ ኢ/ህ/አ/ፓ ያለ አንዳች መንስኤ አባላቱን እርስ በርስ እንዲሳለሉ አላደረገም፡፡

በዚሁ ገፅ ላይ በኢ/ህ/አ/ፓ እንቅሳቃሴ ውስጥ የተልእኮ መክሸፍ አዲስ ነገር አለመሆኑን ይጠቅስና የርሱ ተልእኮ አለመሳካት ግን በአንጀኝነት ሊያስጠረጥረው እንደቻለ ይገልፃል፡፡ እሱ እንዳለው ተልእኮዎች የከሸፉት አንድ ወይም ሁለት ጊዜ ብቻ አይደለም፡፡ በከሸፈ ተልእኮ ላይ የተሳተፉ ሁሉ በአንጀኝነት ተፈርጀዋል ማለት ግን ነጭ ውሸት ነው፡፡ የወልዲያ ተልእኮ መክሸፍን የመሰለ ታላቅ ጉዳት ሲደርስ እንኳ ፓርቲው ስህተቱን የፈለገው በራሱ የአሰራር፣ የእቅድና የዝግጅት ይዘት ውስጥ እንጂ በአንጃዎች ጎራ አልነበረም፡፡ በበርካታ የተሳኩና ያልተሳኩ ተልእኮዎች ላይ ተሳትፈው ላልተሳካላቸው ስራ የአንጃ ሰሌዳ ያልተለጠፈባቸው የኢ/ህ/አ/ፓና የክንፍ ድርጅቶቹ አባላት ዛሬም በህይወት ስላሉ የሀብታሙ ውሸት ወንዝ አያሻግርም፡፡

347 ፍቅረኛው ቢታኒያ ከእብናት አብራው ወደ ጎንደር ብትሄድ የጎንደሩ የኢ/ህ/አ/ፓ ኮሚቴ ገንዘባችንን ይዞ ሱዳን ሊገባ ነው ብሎ በመስጋት ወዲያው እንደሚያስገድለው አስረግጦ ይናገራል። በማከልም ወደ እብናት ሲሄድ ሰላይ እንደተመደበለት፣ ጎንደር ውስጥ ደግሞ የፓርቲው ታጣቂ ክንፍ እንደተከታተለው ይገልፃል፡፡ ይህ እውነት ቢሆን እንኳ የተመደበበትን ሰላይና የሚከታተለውን የታጠቀ ሀይል እንደምን አወቀው?

348 አንድ የቀጣና ኮሚቴ ቦታ ክፍት በመሆኑ ፍቅረኛው ለጊዜው እዚያ እንድትቆይ የተነገራት መሆኑን ይገልፃል፡፡ በገለፃው መሰረት ቢታኒያ ከጥቃት መከላከያ አሀድ ተገልላ ብዙም ሳትቆይ ነበር የቀጣና ኮሚቴ አባል የተደረገችው። እንደሱ ሁሉ የፓርቲውን እርከን ፉት ብላ ወጥታ ካልሆነ በቀር ከቀጣና በታች ባሉ መዋቅሮች - ሌሎችን ብንተዋቸው በንኡስ ሪጅን፣ ሪጂንና ንኡስ ቀጠና - ውስጥ ቆይታ ልምድ ለማዳበር ጊዜ አላገኘችም፡፡ ይልቁንም እሱ በጠቀሰው የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ሰዎች የቱንም ያህል ተሳትፎ ቢኖራቸው በወጣት ክንፉ ውስጥ ይቆዩ ነበር። የማ.ኮ ተለዋጭ አባል ነበርኩ ባዩ ግን በኢ/ህ/አ/ፓ መካከለኛ የአመራር እርከኖች እንኳ ሰርቶ የሚያውቅ አይመስልም፤ ለተወሰነ ጊዜ ሰርቶ ቢሆን ይህን ሀቅ አይስተውም ነበር።

358 የእንጦጦን ፍተሻ ለማለፍ ትእግስት ያልነበረው ይህ ደራሲ አስር ብር ጉቦ ከፍሎ ያመልጣል፡፡ ከዚያ ቀደም ባለው አመት ፍቅረኛው የፀጉር ቅባት ጉብታ ሳትፈተሽ ያለፈችውን የእንጦጦ ኬላ እሱ አስር ብር ጉብቶ አለፈው፡፡ ጉድ ነው! ለካ በወቅቱ ኬላዎችን ማለፍ ይቸግር የነበረው የሚጎባ የፀጉር ቅባት ወይም አስር ብር ላልያዘ ሰው ነበር!

358-363 ፍቅረኛውን ከእስር ቤት እንዴት እንዳስፈታት ሲተርክ ከአስፈቻው ቡድን ደጀኔ ብቻ ወታደራዊ ክሂሎትና የስራ ድርሻ እንደነበረው መደበቅ አልቻለም፡፡ ይህ ተልእኮ ፍፁም ልቦወለድ ነው፤ የወቅቱን አሰራር ምንም የማያንፀባርቅ፡፡ በመጀመሪያ ታሳሪዋ ሊያስፈቷት የሚፈልጉና የሚችሉ ሰዎች ሰላሉዋት ብቻ አትፈታም፡፡

ርምጃው ቢያንስ በበይነ ቀጣና ኮሚቴ ውሳኔ ማግኘት ነበረበት፡፡ ሁለተኛ የማስፈታቱን ተልእኮ የሚወስደው አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆነ የጥቃት መከላከያ አሀድ ብቻ ነው፡፡

## ማጠቃለያ

በዚህ ፅሁፍ መግቢያው ላይ እንደገለፅኩት ደራሲው ያነሳቸውን በርካታ ኩነቶች አንድ በአንድ ነቅሼ አላወጣሁም፤ እሱ ተሳተፍኩበት በሚለው ማ.ኮ አልተሳተፍኩምና፡፡ ነገር ግን ያነሳቸው ጉዳዮች በከፊልም ይሁን በሙሉ እውነት ቢሆኑ እንኳ ተአማኒነት የላቸውም። ከላይ የተዘረዘሩት ነጥቦች ለዚህ በቂ ማስረጃ ናቸው። በይፋ የምናውቃቸውን እውነታዎችና በወቅቱ ኖረን የታዘብናቸውን ሀቆች አዛብቶ፣ ለዋውጦና ራሱ በፈበረካቸው ሁነቶች ተክቶ መፃፉን ለማሳየት ሞክሬያለሁ፡፡ በይፋ የሚታወቁትን መረጃዎች በዚህ መልክ ካቀረበ፣ ጥቂት ሰዎች ብቻ (የማ.ኮ እና ሌሎች ከፍተኛ የአመራር አባላት ብቻ) ሊያውቋቸው ስለሚችሉ ድርጊቶች የፃፈውን እንዴት ማመን ይቻላል፡፡

መፅሀፉ መግቢያ ቢኖረውና በመግቢያው ውስጥ የድርሰቱ አላማና ግቦች በግልፅ ቢሰጡ - የኢ/ህ/አ/ፓን ስህተቶች መዘርዘር፣ የጥፋት ተልእኮውን በምሳሌ ማሳየት፣ በአብዮቱ ወቅት የተጫወተውን ሚና መኮነን፣ ወዘተ. - የተነሱት ነጥቦች ትክክል ቢሆኑም ባይሆኑም እንደግል አመለካከትና አቋም እወስዳቸው ነበር። በዴሞክራቶች ወግ እና ስነምግባር የምቀበለውንና የምቃወመውን ለያይቼ በጨዋነት ለማሳየት እገደድ ነበር፡፡ የሀብታሙ ስራ ግን አላማና ግቡን በግልፅ ለማስቀመጥ ወኔ የለውም፤ የሌለው ደግሞ የፓርቲውን ባህሪና ታሪካዊ ሚና በልቦለድ ሽፋን ጥላሸት ለመቀባት ያለመ እኩይ ተልእኮ በመያዙ ይመስላል። ይህን ተልእኮ ለደራሲው ማን ሰጥቶት ይሆን እላለሁ፤ ቀጣሪ? ፈጣሪ? ወይስ አስቀባጣሪ?

ቸር ሰንብቱ